በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !!!

እንኳን ለዐቢይ ጾም አራተኛ ሳምንት "መፃጉዕ" በሰላም አደረሳችሁ!!!

የዐቢይ ጾም አራተኛ ሰንበት እና ተከትሎት የሚመጣው ሳምንት "መፃጉዕ" ይባላል። "መፃጉዕ" ማለት በዮሐንስ ወንጌል በምዕ. 5 ላይ ታሪኩን የምናገኘው ድውይ መጠሪያ ሳይሆን **'በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ የተያዘ በሽተኛ ወይም ሕመምተኛ'** ማለት ነው። ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ ድውያነ ሥጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን ደግሞ በትምህርት መፈወስ ነበርና ጎባጣዎችን አቅንቷል፤ ሽባዎችን ተርትሯል፤ የዓይን ብርሃን የሌላቸውን ብርሃን ሰጥቷል፤ መስማት ለማይችሉት መስማትን ሰጥቷል፤ ለምጻሞችን አንጽቷል። ቅዱስ ያሬድም በደዌ የተያዙ ወገኖች ሁሉን ቻይ የሆነውን ጌታ ተስፋ ያደርጉ ዘንድ ለማስተማር እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከደዌ የዳኑትን ሰዎች ለማሰብ ይህንን ሳምንት "መፃጉዕ" በማለት ሰይሞታል።
በዚህ ሰንበት በቤተ-ክርስቲያናችን የሚሰበከው **ምስባክ** የሚከተለውን ይመስላል፡-

"እግዚአብሔር ይረድኦ ውስተ ዐራተ ሕማሙ፤
ወይመይጥ ሎቱ ኩሎ ምስካቤሁ እምደዌሁ፤
አንሰ እቤ እግዚኦ ተሣሃለኒ።"
መዝ. ፵፥፫ - ፬

"እግዚአብሔር በደዌ አልጋ ሳለ ይረዳዋል፤
መኝታውንም በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል፤
እኔም አቤቱ ማረኝ እላለሁ።"
መዝ. 40 ÷ 3-4

ምንባባት፡- ገላ. 5 ÷ 1-ፍጻሜ ፤ ያዕ. 5 ÷ 14-ፍጻሜ ፤ የሐዋ. ሥራ 3 ÷ 1-12
በቅዳሴ ጊዜ የሚነበበው ወንጌል፡- ዮሐ. 5 ÷ 1-25

ይህ መፃጉዕ ለ38 ዓመት በአልጋ ላይ ሆኖ በደዌ ሲሰቃይ የኖረ ሲሆን በዚህም ምክንያት ዘመዶቹ ሁሉ ሰልችተው ስለተዉት ማንም ረዳት የለውም፤ ዘመድ ያላቸው ወደ ጸበሉ እያስገቧቸው ሲድኑ እየተመለከተ 38 የመከራ ዓመታትንም አሳልፏል። ነገር ግን ሰው ሁሉ የረሳውን የማይረሳው አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያድነው ዘንድ እርሱ ባለበት መንገድ ማለፍን ወደደ፤ አዳነውም። ነገር ግን ጌታ ይህን ሰው ከማዳኑ በፊት **‹‹ልትድን ትወዳለህን ›› በማለት** ጠይቆታል። እኛም 'ለምን እያወቀ ይጠይቀዋል' የሚል ጥያቄ ልናነሳ እንችላለን። በትርጓሜ ወንጌል እንደተብራራው ብዙ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን የተወሰኑትን እንመልከት።

የመጀመሪያው አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አላወቂ ሥጋን መዋሐዱን ለማጠየቅ ነው። **ሁለተኛው** ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ፍጹም የሆነ ነጻ ፈቃድን መስጠቱን ለማሳየት ሲል ነው። ክርስቶስ ማንኛውንም ነገር ለሰዎች ሲያደርግ የሰዎችን ፈቃደኝነት ጠይቆ ነው። ለዚህ ነው ሁሉም ሰው ጻድቅ ወይም ሁሉም ሰው ኃጥእ ያልሆነው፤ እግዚአብሔር ፈቃዳችንን አይጋፋምና። **ሦስተኛው** ምክንያት ደግሞ ወደፊት ይህ ድውይ በጌታ ላይ ስለሚመሰክር በሚመሰክርበት ጊዜ 'ያለእኔ ፈቃድ ነው ያዳነኝ' ብሎ እንዳይመሰክር ምክንያት ለማሳጣት ነው። **ከእነዚህ በተጨማሪ፡-** ጌታ የተናገረውን ካስተዋልነው ‹‹ልትድን ትወዳለህን ›› አለው እንጂ ‹‹ላድንህ ትወዳለህን ›› አላለውም። በዚህም ጌታችን ትህትናን ያስተምረናል ማለት ነው።

ጌታችን ይህን ማዳን የፈጸመው በሰንበት በመሆኑ አይሁድ እጅግ ተቃውመዋል፤ እነርሱ ከሥራቸው በሰባተኛው ቀን እንደሚያርፉ ሁሉ ልጁንም ከመከራው ዕረፍት በሆነችው በሰንበት ሲያሳርፈው ሊዋጥላቸው አልቻለም። እኛ ግን ".... በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል" እንዳለ ዘማሪው /መዝ. 23÷ 2/፤ በቅዱስ ቃሉም "ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለው .... ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ" /ማቴ. 11÷28/ ያለውን **በማመን ክርስቶስ ሰንበት ዕረፍት መሆኗን ዕረፍት በመስጠት እንደተረጎመ እንጂ እንዳልሻረ እንመሰክራለን።**
እንግዲህ እኛ ክርስቲያኖች ከሥጋዊ ደዌአችን ለመላቀቅ የእግዚአብሔርን ማዳን በቤቱ ሆነን ልንጠብቅ ይገባል፤ ላለብን የነፍስ መፃጉዕነት ደግሞ ኃጢአታችንን ለካህን በመናዘዝ ንስሓ ገብተን ሥጋ ወደሙን ልንቀበል እና በሥጋዊ ደዌ የተያዙ ወገኖቻችንን በመጠየቅ፣ በማስታመም እና በክርስትናቸው በማበርታት አምላካችንን ልናስደስት ያስፈልጋል። **እግዚአብሔር አባታችን በቸርነቱ "ታምሜ ጠይቃችሁኛል" በማለት ቃለ ሕይወትን ያሰማን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን!!!**

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!

የቅዱስ ጳውሎስ ሕክምና ግቢ ጉባኤ ትምህርት ክፍል መጋቢት ፬፣ ፳፻፲፭ ዓ.ም